4ኛው
የሰብአዊ መብቶች
ፊልም
ፌስቲቫል

# በመርኃ ግብሩ የሚቀርቡ የፎቶግራፎች፣ የሥዕል እና አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድር

EHRC Human RIGHTS FILM FESTIVAL
www.ehrc.org

በመርኃ ግብሩ የሚቀርቡ ፎቶግራፎች፣ ሥዕልእና አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድር ......... 1
መግቢያ ........................................................................................................ 1
የጊዜ ገደብ እና ሂደት ........................................................................................ 2
ለውድድሩ የሚነጥበብ ሥራዎችን የመላክ ሂደት ........................................................ 3
ለውድድር የቀረቡ ሥራዎች ግምገማ ...................................................................... 4
አጠቃላይ መመሪያዎች ......................................................................................... 4
ሽልማቶች ....................................................................................................... 5
የፎቶግራፍ ውድድር ......................................................................................... 6
የፎቶግራፍ  ውድድር የቴክኒክ መስፈርቶች ............................................................ 7
የሥዕል ውድድር የቴክኒክ መስፈርቶች .................................................................. 7
የአጫጭር ሥነ ጽሑፎች ውድድር ......................................................................... 8
የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች መስፈርቶች ............................................................. 8
ተጨማሪ ማብራሪያ ........................................................................................... 8

# ዓለም አቀፋ የሰብአዊ መብቶች ቀን የሚታሰብበት 4ኛ ዙር ዓመታዊ የኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል

## በመርኃ ግብሩ የሚቀርቡ ፎቶግራፎች፣ ሥዕልእና አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድር

በ2017 ዓ.ም. በታኅሣሥ 01 ቀን የሚውለው ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ቀንን (December 10) በማስመልከት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በ4ኛው ዙር የፊልም ፌስቲቫል ለዕይታ የሚቀርቡ የፎቶግራፍ፣ የሥዕል እና የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድር አዘጋጅቷል፡፡ በውድድሩ ለመሳተፍ እና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ዝርዝሩን ይመልከቱ፡፡

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) አዘጋጅነት ለ4ኛ ጊዜ የሚካሄደው የሰብአዊ መብቶች ዓመታዊ ፊልም ፌስቲቫል በኢሰመኮ የ2016 በጀት ዓመት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት በከፍተኛ ደረጃ አሳሳቢ በመሆን ከተለዩት ጉዳዮች መካከል በሴቶች ሕይወት (በሕይወት የመኖር መብት) እና በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብቶች ዙሪያ የሚያተኩር ነው፡፡

በሕይወት የመኖር መብት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ተብለው ከሚመደቡት መብቶች አንዱ ሲሆን፣ በሕይወት የመኖር መብት ስለሚያካትታቸው ጉዳዮች እና መብቱ የሚጣስባቸውን ሁኔታዎች በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያ እዚህ ተያይዟል፡፡

ማንኛውም ሰው በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት ያለው ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና የባህል መብቶች በመባል ከተለዩት መብቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ መብቱ በቂ ምግብ የማግኘት መብት ሰፊና በርካታ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች የሚዳስስ መብት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያ እዚህ ተያይዟል፡፡

የዘንድሮ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀንን ለማሰብ የተዘጋጀው አራተኛው የኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ዓመታዊ ፊልም ፌስቲቫል በኅዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም. የሚካሄድ ሲሆን፣ በዝግጅቱ ለዕይታ ከሚቀርቡ የፊልም ውጤቶች በተጨማሪ የተለያዩ የኪነጥበብ ሥራዎች ማለትም የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን፣ ሥዕል እና የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ይገኙበታል፡፡ በዚህ ፌስቲቫል በተለያዩ ከተሞች በሚዘጋጁ መርኃ ግብሮች ላይ ለዕይታ የሚቀርቡ ፎቶግራፎች፣ የሥዕል ሥራዎችና ሥነ ጽሑፎች የተለያዩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በሚሳተፉበት ውድድር ከዝግጅቱ ቀን አስቀድሞ የሚመረጡ ናቸው፡፡

በተለያዩ ከተሞች የሚካሄደው ይህ ፌስቲቫል የፎቶግራፍ፣የሥዕልእና የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድሮችን ያካተተ ሲሆን ፌስቲቫሉ የሚካሄድባቸው ከተሞች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ዘርፎች ከታች በተዘረዘረው መሠረት ውድድሩ የሚከናወን ይሆናል፦

| | ከተማ | የውድድር ዘርፍ | ውድድሩ የሚያተኩርበት ጭብጥ |
|---|---|---|---|
| 1. | አዲስ አበባ | የፎቶግራፍ እና የሥነ ጽሑፍ ውድድር | የሴቶች ሕይወት እና በቂ ምግብ እና ውሃ የማግኘት መብት |
| 2. | አዳማ | የፎቶግራፍ ውድድር | በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት |
| 3. | አርባምንጭ | የፎቶግራፍ ውድድር | በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት |
| 4. | አሶሳ | የሥዕል ውድድር | የሴቶች ሕይወት |
| 5. | ባሕር ዳር | የሥዕል ውድድር | የሴቶች ሕይወት |
| 6. | ሃዋሳ | የፎቶግራፍ ውድድር | በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት |
| 7. | ጋምቤላ | የሥዕል ውድድር | የሴቶች ሕይወት |
| 8. | ጅግጅጋ | የፎቶግራፍ ውድድር | በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት |
| 9. | ጅማ | የፎቶግራፍ ውድድር | በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት |
| 10. | መቀሌ | የሥዕል ውድድር | የሴቶች ሕይወት |
| 11. | ሰመራ | የሥዕል ውድድር | በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት |

## የጊዜ ገደብ እና ሂደት

የውድድር ጊዜው ጥቅምት 01 ቀን 2017 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2017 ዓ.ም. እኩለ ለሊት (በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከለሊቱ 6፡00 ሰዓት) ድረስ ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች በእነዚህ ቀናት ለውድድር የሚያቀርቧቸውን የኪነጥበብ ሥራዎች ከሥር በተመለከተው አድራሻ፣ እዚህ የተያያዘውን ቅጽ በመሙላት መላክ ይችላሉ። ለውድድር የተላኩ የኪነጥበብ ሥራዎች በሁለት ዙር የሚገመገሙ ይሆናል።

**በመጀመሪያው ዙር፡** በኅዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም. ለሚውለው የኢሰመኮ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል ዝግጅት ለዕይታ የሚቀርቡ የኪነጥበብ ሥራዎች ይመረጣሉ፤

**በሁለተኛው ዙር፡** በኅዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም. ለሚውለው ዝግጅት በየከተማው ለዕይታ እንዲቀርቡ ከተመረጡ ሥራዎች መካከል ከአንደኛ እስከ አስረኛ ደረጃ የወጣላቸው የኪነጥበብ ሥራዎች እጩ የሚደረጉበት ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃ የሚመደቡ የኪነጥበብ ሥራዎች ይመረጣሉ።

ከአንደኛ እስከ አስረኛ የወጡ  እንዲሁም ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ የተመደቡ የኪነጥበብ ሥራዎች ውድድሩ በተካሄደባቸው ከተሞች በሚዘጋጀው የመክፈቻ ዝግጅት ላይ የሚገለጹ ሲሆን፣ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ የተመደቡ የኪነጥበብ ሥራዎች እያንዳንዳቸው በመድረኩ ላይ በመቅረብ ይሸለማሉ።

ለሁሉም የኪነጥበባ ሥራዎች ውድድር ተሳታፊዎች የተሳትፎ ዕውቅና ሰርተፊኬት ይሰጣል።

እንዲሁም ተጨማሪ ተያያዥ ማበረታቻዎች እንደ አግባብነቱ ለተሳታፊዎች ይገለጻል::

ሆኖም ከኢሰመኮ እሴቶች እና መርሖች አንዱ ግልጽነት በመሆኑ በየከተማው በውድድሩ የተሳተፉ ግለሰቦች እና ተቋማት፣ እንዲሁም የቀረቡት የኪነጥበብ ሥራዎች በሙሉ በኢሰመኮ ድረገጽ እና ማኅበራዊ ትስስር ገጾች እንዲሁም በተለያዩ አመቺ መንገዶች የሚገለጹ ይሆናሉ::

## ለውድድሩ የኪነጥበብ ሥራዎችን የመላክ ሂደት

ከጥቅምት 01 ቀን 2017 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2017 ዓ.ም. (እኩለ ለሊት ወይም በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከለሊቱ 6፡00 ሰዓት) ድረስ ለውድድር የሚቀርበውን የኪነጥበብ ሥራ እንዲሁም የተሞላ እና የተፈረመበት የተሳትፎ ቅጽ በማያያዝ ከዚህ በታች በተመለከተው መልኩ መላክ ይችላሉ::

| | |
|---|---|
| በኢሜል | filmfest@ehrc.org |
| በቴሌግራም | @EthioHRC |
| **በሚከተሉት አድራሻዎች በሚገኙት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ቢሮዎች በአካል በመገኘት** | |
| አዲስ አበባ | ሰንሻይን ታወር ቁጥር 5፣ መስቀል አደባባይ አለፍ ብሎ ቦሌ መንገድ፣ ሀያት ሬጀንሲ ሆቴል አጠገብ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ |
| አሶሳ | ወረዳ 1 – መብራት ኃይል ቢሮ ፊት ለፊት፣ ወደ አሶሳ አጠቃላይ ሆስፒታል በሚያቋርጠው መንገድ፣ አሶሳ፣ ኢትዮጵያ<br>+25157 775 08 50/ +25157 775 00 55/ +25157 775 06 90 |
| ባሕር ዳር | ዳግማዊ ምኒሊክ ክፍለ ከተማ ፍኖተ ቀበሌ፣ አረጋውያን ሕንጻ 3ኛ ፎቅ፣ ባሕር ዳር፣ ኢትዮጵያ<br>+25158 226 24 71 |
| ጋምቤላ | ከሞቢል ፊት ለፊት/ከዊቡር የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጎን፣ ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ<br>+25147 551 13 76/ +25147 551 22 06 |
| ሃዋሳ | መናኸሪያ — ሚለንየም መንገድ፣ ወደ ሪፈራል ሆስፒታል በሚወስደው መንገድ፣ ቅዱስ ገብርኤል ሕንጻ፣ 3ኛ ፎቅ<br>ሃዋሳ፣ ኢትዮጵያ<br>+25146 220 59 74 |
| ጅግጅጋ | ከቀበሌ 10 ጽሕፈት ቤት አጠገብ፣ ከፋራህ መኀል ትምህርት ቤት ፊት ለፊት፣ ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ<br>+25125 278 42 14/ +25125 278 16 84 |
| ጅማ | አዌቱ መንደራ ቀበሌ፣ ጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አጠገብ አቡነ እስጢፋኖስ ሕንጻ ላይ፣ ጅማ፣ ኢትዮጵያ<br>+25147 111 40 43/ +25147 111 64 40 |
| ሰመራ | በሰመራ ሎጊያ መንገድ፣ ወደ ሰመራ አየር መንገድ መገንጠያ አዲሱ ሕንጻ ላይ፣ ሰመራ፣ ኢትዮጵያ |

ከላይ ከተጠቀሱት የመላኪያ አማራጮች ውጪ በኢሰመኮ ድረገጽ አልያም በማኅበራዊ ሚዲያ አድራሻዎች፣ አልያም በሌላ መንገድ የሚላኩ የኪነጥበብ ሥራዎች በውድድሩ አይካተቱም ወይም ከውድድሩ ውጪ ይሆናሉ። የተሟላ የተሳትፎ ቅጽ ያላያያዙ የኪነጥበብ ሥራዎች በውድድሩ አይካተቱም ወይም ከውድድሩ ውጪ ይሆናሉ። በሲዲ (CD) ወይም በፍላሽ ዲስክ (USB) ለውድድር ከሚቀርበው የኪነጥበብ ሥራ ውጪ ሌላ ምንም ዐይነት ይዘት ሊኖር አይገባም። ግልጽ ያልሆነ፣ የማይነበብ ወይም ሌሎች የቴክኒክ ግድፈቶች ያሉበት ፋይል አልያም ከሌሎች ይዘቶች ጋር የሚላኩ የኪነጥበብ ሥራዎች ከውድድር ውጪ የሚደረጉ ሲሆን፣ ለዚህም የኢሰመኮ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## ለውድድር የቀረቡ ሥራዎች ግምገማ

የዓመታዊው የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል ዋነኛ ዓላማ የኪነጥበብን እና የሰብአዊ መብቶችን ትስስር ለማጠናከር እና በሁለቱ ዘርፎች መካከል ያለውን ጥምረት በተመለከተ ግንዛቤ ለማስፋፋት፣ እንዲሁም ኪነጥበብ "ሰብአዊ መብቶች ባህል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት" የሚለው የኢሰመኮ ራዕይ መሳካት ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽዖ ለማስታወስ ነው። በተጨማሪም የፊልም ፌስቲቫሉ የኪነጥበብ ሥራዎችን በውድድር መልኩ ሲጋብዝ ይህ ሁለተኛው ጊዜ ሲሆን፣ የዚህ ዙር ዓላማ በርካታ ተወዳዳሪዎችን መጋበዝ እና እንዲሳተፉ ማበረታታት ነው።

በመሆኑም ለውድድሩ የሚቀርቡ ሥራዎች የቴክኒክ መስፈርቶች ቀለል ያሉ እና በአብዛኛው በተለይም ትኩረት ከተደረገባቸው በሴቶች ሕይወት (በሕይወት የመኖር መብት) እና በቂ የሆነ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት ጋር ባላቸው ተያያዥነት የሚገመገሙ ይሆናሉ።

ለዚህ ሂደት የጥበብ ሥራዎቹን የቴክኒክ መስፈርት የሚገመግም አንድ ባለሞያ፣ ከሦስተኛው ዙር አሸናፊዎች፣ በተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ዘርፎች (በሲቪል እና ፖለቲካ፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ፣ በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያን፣ እንዲሁም በስደተኞች፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና በፍልሰተኞች መብቶች) የሚሠሩ የኢሰመኮ እና የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሙያዎች፣ የኢሰመኮ የሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ሥራ ክፍል ባለሙያዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሥራ ክፍሎች ባለሙያዎች የተካተቱበት፣ ለመጀመሪያ ዙር ግምገማ የ5 ገምጋሚዎች ፓነል፣ ለሁለተኛ ዙር ግምገማ የ7 ገምጋሚዎች ፓነል ይቋቋማሉ።

ገምጋሚዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የማወዳደሪያ መስፈርቶች ለኪነጥበብ ሥራዎቹ ነጥብ የሚሰጡ ሲሆን፣ ሁሉም ገምጋሚዎች የሰጡት ነጥቦች ድምር አማካይ የኪነጥበብ ሥራው የመጨረሻ ውጤት ይሆናል። ሁለት የኪነጥበብ ሥራዎች ተመሳሳይ ውጤት በሚያገኙበት ጊዜ በገምጋሚ ፓነሉ አብላጫ ድምጽ የሚወሰን ይሆናል። የገምጋሚ ፓነሉ ውሳኔ የመጨረሻ ነው።

## አጠቃላይ መመሪያዎች

1. በሚከተሉት የማኅበረሰብ ክፍሎች (ልዩ ትኩረት የማኅበረሰብ ክፍሎች) ላይ ለሚያተኩሩ ለውድድር የሚቀርቡ ሁሉም የኪነጥበብ ሥራዎች ለውድድሩ መስፈርቶች ከሚሰጡ ነጥቦች በተጨማሪ የማበረታቻ ነጥቦች (bonus) ያገኛሉ፦
    - በሕፃናት እና ታዳጊዎች (ዕድሜያቸው ከ18 ያልበለጡ)
    - በሴቶች
    - በአረጋውያን
    - በአካል ጉዳተኞች

- በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ወይም በስደተኞች

2. ማንኛውም ግለሰብ፣ ማናቸውም መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሚዲያ እና የኮሙኒኬሽን ድርጅት፣ የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ የመገናኛ ብዙኃን ወይም የስልጠናና ትምህርት ሰጪ ተቋማት ወይም በተዘረዘሩት ተቋማት የሚሠሩ፣ የሚሰለጥኑ፣ የሚማሩ እና የሚያስተምሩ ግለሰቦች በሁሉም የውድድር ዘፎች እራሳቸውን ወክለው/በግል መሳተፍ ይችላሉ::
3. በውድድሩ ለመሳተፍ ኢትዮጵያዊ መሆን ያስፈልጋል:: ውድድሩ የሀገር ውስጥ ባለሙያዎችን እና ተቋማትን ለማበረታታት እና ዐቅም ለመገንባት ያለመ እንደመሆኑ በሀገር ውስጥ የተመዘገቡ፣አልያም ተቀማጭነታቸውን ኢትዮጵያ ያደረጉ ቢሆኑም አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ለሆኑ የሲቪክ ማኅበረሰብም ሆነ ሌሎች ተቋማት ክፍት አይደለም::
4. በውድድር ለመሳተፍ ምንም ዐይነት ክፍያ አይጠየቅም::
5. የኢሰመኮ ሠራተኞች በሁሉም የውድድር ዘርፎች መሳተፍ የሚችሉ ሲሆን፣ የጥበብ ሥራዎቹ ለዕይታ ለመቅረብ ብቁ ሆነው ከተገኙ ሊመረጡ ይችላሉ:: ሆኖም በውድድሩ ለሽልማት እጩ ከሚሆኑ የጥበብ ሥራዎች መካከል አይካተቱም::
6. በአንድ የውድድር ዘርፍ የኪነጥበብ ሥራውን ያቀረበ ተሳታፊ በሌላ ዘርፍ ተጨማሪ የጥበብ ሥራ ለውድድር ማቅረብ አይችልም:: ስለሆነም ተሳታፊዎች በአንድ ዘርፍ ብቻ የሚወዳደሩ ይሆናል::
7. በተጨማሪም አንድ ተሳታፊ በሚወዳደርበት ዘርፍ ከአንድ በላይ የኪነጥበብ ሥራ ማወዳደር አይችልም::
8. ተሳታፊዎች ለሌሎች ውድድሮች ያቀረቧቸውን የኪነጥበብ ሥራዎች ለዚህ ውድድር ማቅረብ ይችላሉ::
9. የውድድሩ አዘጋጆች ተጨማሪ ማብራሪያ ወይም መረጃ አልያም ከውድድሩ ጋር በተያያዘ ሌላ ምክንያት ተሳታፊዎችን በተሳትፎ ቅጹ ባስቀመጡት አድራሻ ለማግኘት ሞክረው፣ ተሳታፊዎች በተገለጸው አድራሻ በተገቢው ጊዜ በማይገኙበት ወይም ምላሽ በማይሰጡበት ወቅት የውድድሩ አዘጋጆች ለውድድር የቀረበውን ሥራ ከውድድሩ ውጪ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ይህም የኢሰመኮ ውሳኔ የመጨረሻ ነው::
10. ተሳታፊዎች ከሚወክሉት ተቋም ወይም ከእራሳቸው ውጪ ያሉ (የሦስተኛ ወገንን) የኪነጥበብ/ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን ለውድድሩ ማቅረብ አይችሉም:: የኢሰመኮ ይህንን የማረጋገጥ ሙሉ መብት የተጠበቀ ነው::
11. በአንድ የውድድር ዘርፍ በብዛት እና በብቁነት በቂ ተወዳዳሪ አለመኖሩ ከድምዳሜ ላይ ከተደረሰ፣ የውድድሩ አዘጋጆች የውድድር ዘርፉን ሊሰርዙ ይችላሉ:: ይህም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል:: ሆኖም ኢሰመኮ በተሰረዘው የውድድር ዘርፍ የተላኩ የኪነጥበብ ሥራዎችን ለተሳታፊዎች የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ በተሳትፎ መመሪያ እና ደንቦች አንቀጽ (2) እና (8) መሠረት ጥቅም ላይ ማዋል አይችልም::

## ሽልማቶች

- የውድድሩ ተሳታፊዎች በሙሉ የተሳትፎ ዕውቅና ሰርተፍኬት የሚያገኙ ይሆናል፤
- ለውድድሩ የቀረቡ የኪነጥበብ/የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች በሙሉ እንደ አግባብነታቸው ለተለያዩ የኢሰመኮ እና የአጋር ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች መረጃዎች፣ ሪፖርቶች፣ የማስተማርያ እና የኮሙኒኬሽን ሰነዶች ወይም የኦድዮ ቪዥዋል ሥራዎች የሚውሉ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት ለኪነጥበብ ሥራ አቅራቢው ሙሉ ዕውቅና ይሰጣል፤
- ከዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫሉ ባሻገር ከአንድ እስከ አስረኛ ደረጃ የተመደቡ የኪነጥበብ/የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች በተለያዩ ሀገር አቀፍ እና የክልል መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ አግባብ ባላቸው የኢሰመኮ፣ የሲቪክ ማኅበረሰብ እና ሌሎች መድረኮች እንዲሰራጩ፣ እና ለዕይታ እንዲበቁ የሚደረግ ይሆናል:: በዚህ ወቅት ለኪነጥበብ ሥራ አቅራቢው ዕውቅና

የሚሰጥ ይሆናል፤

- በዝግጅቱ ለዕይታ የሚቀርቡ የኪነ ጥበብ/ ሥነ ጽሑፍ ሥራ አቅራቢዎች/ ተሳታፊዎች ተጨማሪ የማስተዋወቂያ እና በተቻለ መጠን የተለያዩ የዐቅም ግንባታ እና የሥራ ዕድል አጋጣሚዎችን ለመፍጠር ኢሰመኮ ጥረት የሚያደርግ ይሆናል፤
- ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ የተመደቡ የፎቶግራፍ፣ የሥዕል እና የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች እንደየደረጃቸው በሚከተለው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የገንዘብ ሽልማት (በኢትዮጵያ ብር) የሚያገኙ ይሆናል።

| ደረጃ | የፎቶግራፍ እና ሥዕል ውድድር አሸናፊዎች | የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ውድድር አሸናፊዎች |
|---|---|---|
| አንደኛ | 25 ሺህ | 30 ሺህ |
| ሁለተኛ | 20 ሺህ | 25 ሺህ |
| ሦስተኛ | 15 ሺህ | 20ሺህ |
| ልዩ ትኩረት የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ አተኩረው የተዘጋጁ የኪነጥበብ ሥራዎች ማበረታቻ/ ቦነስ የገንዘብ ሽልማት፡ በሁሉም ዘርፍ እና በሁሉም ደረጃ፡ 3ሺህ ብር። | | |

ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆኑ ተሳታፊዎች በቀጣይ ዙር የኢሰመኮ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል በሚዘጋጁ ውድድሮች የሚቀርቡ የኪነጥበብ/ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ገምጋሚ ፓነል አባል እንዲሆኑ ጥሪ ይደረግላቸዋል።

ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ሽልማቶችን ወደ ገንዘብ ሽልማት የመቀየር አማራጭ የለም።

ገንዘብ ነክ ለሆኑ እና ላልሆኑ ሽልማቶች በሀገሪቱ ሕግ መከፈል ለሚኖርባቸው ቀረጦች እና ሌሎች ግብሮችን፣ ቅጣቶችን፣ ክፍያዎችን ወይም የአስተዳደር ጉዳዮችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኃላፊነት አይወስድም።

## የፎቶግራፍ ውድድር

ይህ የውድድር ዘርፍ ምግብና ውሃ በማግኘት መብት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ተሳታፊዎች በቂ ስለሆነ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት የተለያዩ ጥያቄዎችን የሚያጭሩ፣ ሐሳብ የሚሰጡ፣ የመብቱ መከበር ወይም መጣስ በተጨባጭ ምን እንደሚመስል የሚገልጹ እና ለማሰላሰል የሚጋብዙ ምስሎችን (ፎቶግራፎችን) የሚያቀርቡበት ነው።

በቂ የሆነ ምግብ እና ውሃ ማለት ምን ማለት ነው? ምግብ እና ውሃ የሌለው ሰው አኗኗር ምን ይመስላል? ምግብና ውሃ የማግኘት መብት ለሴቶች እና ለወንዶች አንድ ዐይነት ትርጉም አለው? የአካል ጉዳተኞች ምግብና ውሃ የማግኘት መብት ምን ይመስላል?

ይህ የፎቶግራፍ ውድድር ዘርፍ እነዚህን እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በምስል ለመግለጽ እና ለማሰላሰል የሚጋብዝ ነው። በዚህ የውድድር ዘርፍ በጀማሪም ይሁን ልምድ ባለው

ባለሙያ ለሚቀርቡ የኪነጥበብ ሥራዎች የመወዳደሪያ መስፈርቶች ተመሳሳይ ናቸው።

## የፎቶግራፍ ውድድር የቴክኒክ መስፈርቶች

1) ለውድድር የሚቀርበው ፎቶግራፍ ለዘርፉ ከተመደበው ጭብጥ/ ርዕሰ ጉዳይ ጋር (በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት) ተያያዥነት ያለው ሊሆን ይገባል።
2) በዚህ ዘርፍ የሚቀርቡ የፎቶግራፍ/ የኪነጥበብ ሥራዎች ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ የተነሱ/የተወሰዱ ሊሆኑ ይገባል።
3) ለዚህ ውድድር የሚቀርቡ የኪነጥበብ ሥራዎች ከ1 ሜጋ ባይት ያላነሱ እና ከ5 ሜጋ ባይት ያልበለጡ ሊሆኑ ይገባል።
4) በ JPEG ሴቭ የተደረጉ እና በተቻለ መጠን ለኅትመት አመቺ በሆነ ከፍተኛ የጥራት (ሪዞሉሽን) ደረጃ ሊሆኑ ይገባል።
5) ለፎቶግራፍ ሥራ ከሚያስፈልገው የአርትዖት (editing) ሥራ በተጨማሪ፣ መጠነኛ በሆነ መልኩ ፎቶግራፉን ለማሳመር የሚደረጉ (digital manipulations) ሥራዎች ተቀባይነት አላቸው። ሆኖም እነኚህ ለውጦች ምን እንደሆኑ እና ለምን ዓላማ እንደተሠሩ በተሳትፎ ቅጹ ላይ በግልጽ ሊመላከት ይገባል። የውድድሩ አዘጋጆች ይህንን በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያ ለተሳታፊው ሊያቀርቡ ይችላሉ። እንዲሁም ተጨማሪ ሥራዎች ያልተሠራበትን (ኦሪጂናል) ፎቶግራፍ እንዲላክ ሊጠይቁ ይችላሉ።
6) ተሳታፊው የሚጠቀመው ካሜራ ቢያንስ 3000 ፒክሰል (ወደ ጎን) እና 300 DPI/PPI setting ሊሆን ይገባል። በሞባይል/ተንቀሳቃሽ ስልክ የሚነሱ ፎቶግራፎች ይህንን መስፈርት ማሟላት የሚጠበቅባቸው ባይሆንም፣ ለውድድር ተቀባይነት የሚኖራቸው ከፍተኛ ጥራት (high resolution) ያላቸው እና ከተመደበው ጭብጥ/ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ከሆነ ብቻ ነው።
7) በተለይ በአንድ ሰው ላይ የሚያተኩሩ ፎቶግራፎች ከሆኑ የዛን ሰው ሙሉ ፈቃድ ማግኘት፣ ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ደግሞ በሕግ ሙሉ መብት ያለውን ወይም የአሳዳጊ ሙሉ ፈቃድ ማግኘትዎን ያረጋግጡ።
8) Collage ወይም በአንድ ፍሬም በርካታ ምስሎችን የያዘ ፎቶግራፍ በውድድሩ አይካተትም። ለውድድር በሚቀርበው ፎቶግራፍ ላይ ፊርማ፣ watermark፣ overlay እና የመሳሰሉትን ምልክቶች ወይም ጽሑፎች መጨመር አይገባም።

## የሥዕል ውድድር የቴክኒክ መስፈርቶች

ከላይ ለፎቶግራፍ ውድድር የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በሥዕል የሚወዳደሩ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማማሏት አለባቸው

- የተፈቀዱ የሥዕል ዐይነቶች፡-
  - ማንኛውም 2D ሥዕል ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ በእርሳስ፣ በቻርኮል፣ በየውሃ ወይም የዘይት ቀለሞች፣ ባለቀለም እርሳሶች፣ አክሪሊክስ ቀለሞች እንዲሁም በወረቀት ወይም ዲጂታል ሚዲያዎች በተጨማሪ በሸራ ላይ የተሠሩ ሥዕሎች ተቀባይነት አላቸው።
- ገደቦች፡-
  - 3D የተሠሩ ወይም ቁሳቁሶችን የሚያካትቱ ቅርጻ ቅርጾች ወይም ድብልቅ የሆኑ ሥራዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።
  - ተሳታፊዎች ከኪነጥበብ አቅርቦቶች ጋር የተያያዙ ወጪዎችን መሸፈን የራሳቸው ኃላፊነት ሲሆን እንደ ሸራ፣ ቀለም፣ ብሩሽ፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ሥራቸውን ለመፍጠር ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች ማካካሻ ወይም የቅድሚያ ክፍያ አይሰጥም።
- የመጠን መስፈርቶች፡
  - በአካል ለሚቀርቡ ሥራዎች፡-

- በወረቀት የሚቀርቡ ሥዕሎች፣ የሚፈቀዱት መጠኖች A3 ወይም A4 ናቸው::
- ለሸራ ሥዕሎች ከፍተኛው መጠን 50 x 70 ሴ.ሜ ነው::

○ በዲጂታል ለሚላኩ ሥራዎች:-

- በከፍተኛ ጥራት ስካን የተደርጉ ወይም በጥራት ፎቶግራፍ የተነሱ መሆን አለባቸው:: ምስሎቹ በበቂ ብርሃን የተነሱ፣ ግልጽ እና ከጥላዎች እና ሌሎች የምስሉን ጥራት ከሚያጓድሉ ነገሮች የፀዱ መሆን አለባቸው::

## የአጫጭር ሥነ ጽሑፎች ውድድር

ይህ የውድድር ዘርፍ በሕይወት የመኖር መብት በተለይም በሴቶች ሕይወት እና በቂ ምግብና ውሃ ማግኘት ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ተሳታፊዎች ስለ ሴቶች ሕይወት እንዲሁም በቂ ምግብና ውሃ የማግኘት መብት ላይ የተለያዩ ጥያቄዎችን የሚያጭሩ፣ ሐሳብ የሚሰጡ፣ የመብቱ መከበር ወይም መጣስ በተጨባጭ ምን እንደሚመስል የሚገልጹ እና ለማሰላሰል የሚጋብዙ አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን የሚያቀርቡበት ነው::

ይህ የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድር ዘርፍ የሚሸፍነው ርዕሰ ጉዳዩ ሰፊ እንደመሆኑ መጠን የሥነ ጽሑፍ ውጤቱ በግጥም ወይም በስድ ንባብ/ ጽሑፍ መልክ ሊቀርብ ይችላል:: በዚህ የውድድር ዘርፍ ልብ ወለድ አልያም በእውነተኛ ታሪክ ላይ መሠረት ያደረጉ ታሪኮችን/ ክስተቶችን ማቅረብ የሚቻል ይሆናል:: እንደ ሌሎቹ የውድድር ዘርፎች ሁሉ በዚህ ውድድር መመሪያ እና ደንቦች በተገለጸው መሠረት ማስታወቂያ የሚያካትቱ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ከውድድሩ ውጪ ይደረጋሉ::

በዚህ ዘርፍ በጀማሪም ይሁን ልምድ ባለው የሥነ ጽሑፍ ባለሙያ የተዘጋጁ እና ለውድድር የሚቀርቡ አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የመወዳደሪያ መስፈርቶች ልዩነት የላቸውም::

## የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች መስፈርቶች

1) አጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ግጥም ወይም ዝርው ጽሑፍ ሊሆኑ ይችላሉ::
2) ለውድድር ዘርፉ ከተመደበው ጭብጥ/ ርዕሰ ጉዳይ (በሕይወት የመኖር መብት (የሴቶች ሕይወት) እና ከበቂ የምግብና የውሃ መብት) ጋር የተያያዘ መሆን አለበት::
3) የአጭር ሥነ ጽሑፉ ርዝመት ከሁለት ገጽ ያላነስ እና ከአራት ገጽ ያልበለጠ ወይም ከ600 ቃላት ያላነስ እና ከ1200 ቃላት ያልበለጠ ሊሆን ይገባል::
4) በዚህ ዘርፍ የሚቀርቡ ሥራዎች ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ የተጻፉ ሊሆኑ ይገባል::
5) በማንኛውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተጻፈ አጭር ጽሑፍ ለውድድሩ መቅረብ ይችላል:: ሆኖም ጽሑፉ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተተርጉሞ አባሪ ሆኖ ሊቀርብ ይገባል::
6) ጽሑፉ በMS word ተጽፎ መቅረብ ያለበት ሲሆን ርዕሱ በ14 ይዘቱ ደግሞ በ 12 font size እና በነጠላ መስመር ክፍተት (single line spacing) መሆን አለበት::

## ተጨማሪ ማብራሪያ

በእነዚህ መመሪያዎች እና ደንቦች ስለተጠቀሱ ሂደቶች ወይም መረጃዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት filmfest@ehrc.org ይላኩልን::